

# ወደ እንግሊዝ አገር በገቡ የምስራቅ አፍሪካ ወጣት ስደተኞች የፆታ ግንኙነት እውቀት እና ህብረተሰባዊ ውህደት ከፍ ለማድረግ

## የአጭር ሥነ ጽሑፍ ውድድር

ከብሔራዊ ሎተሪ በተገኘ ድጋፍ በፔንሃ (PENHA) የተዘጋጀ

**ቋንቋዎች፡ አማርኛ፣ አረብኛ፣ እንግሊዘኛ፣ ሶማሊኛ፣ ኦሮሚኛ፡ ትግርኛ እና ሌሎች የአፍሪካ ቀንድ ቋንቋዎች**

የማስረከቢያ የመጨረሻ ቀን: **30/04/2023**

የምስራቅ አፍሪካ ስደተኞች እንግሊዝ እንደደረሱ በርካታ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ያጋጥሟቸዋል። በቋንቋ አለመቻል፣ የባህል ልዩነቶች እና የእንግሊዝ አገር ህግን ካለመረዳት የተነሳ ብዙዎቹ የተለያዩ ችግሮች ያጋጥሟቸዋል፣ በፆታዊ ጥቃት ሰለባ መሆንን ወይም በሌሎች በዚህ በጾታዊ ጥቃት መከሰስን ጨምሮ። እነዚህም ሁኔታዎች ወደ እስራት እና ወደ ጾታዊ ጥቃት አጥፊዎች መመዝገቢያ ሊያመራቸው ይችላል። ስለዚህ፣ ከፆታዊ ጥቃት ጋር የተያያዙ ስምንት ታሪኮችን፣ የ(ወሲባዊ) ፍቃድ ህጋዊ ዕድሜ፣ እና በትውልድ ሀገርዎ እና በእንግሊዝ መካከል ያለውን የፆታ ግንኙነት የመረዳት ልዩነትን የሚያስረዳ መሆን አለበት። በእንግሊዝ አገር በመጡ ወጣቶች መካከል የሚካሄደው ይህ ግንዛቤአዊ የሥነ ጽሑፍ ውድድር ለ 'Beyond managing expectations: Supporting the integration of refugees in Kent'' ፕሮጀክት ላይ አስተዋፅኦ ያደርጋል።

እነዚህ ወጣቶች የተሻለ የወደፊት ሁኔታን የመገንባት አቅም አላቸው፣ እና ይህ ከጾታዊ ግንኙነት ጋር በተያያዙ ግላዊ ልምዶቻቸው ላይ እንዲያንፀባርቁ እድል ሊፈጥርላቸው ይችላል። ይኸውም ተግባር ታሪኮቻቸውን ወይም የሌሎችን ታሪክን በመጻፍ ሊያሳትፋቸው ይችላል፣ ይህም ስለሥርዓተ፡ፆታ እና ስለ ፃታዊ ግንኙነት ያላቸውን ግንዛቤ ለማሳደግ፣ ሊከሰቱ የሚችሉ ወንጀሎችን ለመከላከል፣ የሚያጋጥሟቸውን ስሜታዊ ችግሮችን ለመቋቋም እና በሚያስፈልግበት ጊዜ ምክር እና ህጋዊ እርዳታን እንዲፈልጉ ለማበረታታት ያስችላል።

***መመሪያ***

- በሥነ ጽሑፍ ሊሸፈኑ የሚችሉ ርዕሰ ጉዳዮች፡ ጾታዊ ትምህርት፣ ጾታዊ ጥቃት፣ የፈቃድ ዕድሜ፣ የባህል ልዩነቶች እና ከግንኙነት ጋር የተያያዙ ግንዛቤዎች፣ ወዘተ። ታሪኩ ወደ እንግሊዝ በአደርጉት ጉዞ ወይም ወደ እንግሊዝ ከገቡ በኋላ ከአጋጠማቸዉ ልምድ ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን ሊያመለክት ይችላል።
- ከላይ ከተጠቀሱት ርእሶች ጋር የተያያዘ ባለ 1-2 ገጽ ወይም 1,000 ቃላት የያዘ ታሪክ ማዘጋጀት። ታሪኩ በጣም አጭር እና በዋናነት በጭብጡ ላይ ማተኮር አለበት። ከ 2 ገጽ በላይ የሆኑ ታሪኮች ኮሚቴው ግምገማ ውድቅ ይሆናሉ።
- ታሪኩ በእንግሊዝኛ፣ በአማርኛ፣ በአረብኛ፣ በአፋን ኦሮሞ፣ በትግርኛ፣ በሶማሊኛ እና በሌሎች የአፍሪካ ቀንድ ቋንቋዎች ሊጻፍ ይችላል።
- የዕድሜ ቡድን፥ 16-25። ፀሐፊው በዚህ የዕድሜ ክልል ውስጥ ቢሆን ይመረጣል፣ ነገር ግን ውድድሩ ለማንም ክፍት ነው፣ እንደ ወጣቶችን እንደሚረዱ ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞችን ይጨምራል።
- እያንዳንዱ ተወዳዳሪ በአንድ የሥነ ጽሑፍ ብቻ መወዳደር ይችላል - እና መግባት ያለበት በኦን ላይን ብቻ ነዉ።
- የባለቤትነት መብት፡- ፀሀፊው/ዋ የፅሁፉ ህጋዊ ባለቤት ነዉ/ናት።
- የሥነ ጽሑፍ ተወዳዳሪዎች ከእንግሊዝ አገር መሆን አለባቸው።
- የጥበብ እና የሥነ ጽሑፍ ስራዎቻቸው ይገመገማሉ፡ እና ምርጥ ታሪኮች ይሸለማሉ። ይኸውም የተወዳደረው የሥነ ጽሑፍ ሥራህ ከተመረጠ £100 ያሸልማል።
- የተመረጡት ታሪኮች እንደ ትንንሽ መጽሐፍ በዲጂታል መልክ በግንቦት 2023 ይታተማሉ።
- ለመወዳደሪያ ክፍያ አያስፈልግም።
- የማስረከቢያ የመጨረሻ ቀን፥ 30.04.2023

ተጠሪ ወይም የመወዳደርያ ጽሑፍ ለማቅረብ፡- PENHA፣ በረከት ኢሜል: info@penhanetwork.org

PENHA
MIGRATION, YOUTH & DEVELOPMENT PROGRAMME

COMMUNITY FUND